# የሚሳደቡ ደካሞች ናቸው መወያየት አይችሉምና.....

ለአቶ ብርሃን ካሳይ የተሰጠ መልስ

ተኮላ መኮንን
tekolamekonen@yahoo.com

ሃገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
ነገራችን ሁሉ የእምቧይ ካብ የእንቧይ ካብ።
        ዮፍታሄ ንጉሴ

በተወለድንባት ውድ ሃገራችን ኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን ማናቸውንም በጎ ሆነ መጥፎም ዜና በየፊናችን ሁላችንም መከታተላችን እሙን ነው። ነገሮቹን የምንረዳበትና የምንቀበልበት ሁኔታ ግን ከግለሰብ ግለሰብ መለየቱን የምንስማማበት ጉዳይ ይመስለኛል። በሃሳብ መለየት ደግሞ ጥሩን በመናፈቅ የመነጨ ከሆነ ያመለካከት ልዩነት ነውና እንደ ጤነኛ ጎን ወስደነው እናልፋለን። እንደ እኔ አመለካከት ደግሞ ማንም ሀገሬን ልጉዳ ብሎ ይነሳል ብዬ አልጠረጥርም። አንዳንዱ ከግንዛቤ ጉድለት፣ አንዳንዱ ከመረጃ እጥረት፣ ሌላው ከርእዮተ ዓለም ልዩነት በመንደንደር የሚሰማውን ለመግለጽ ይነሳ ይሆናል እንጂ። ስልጣን ካልጨበጥኩ ሁሉንም አወግዛለሁ፣ በጉልበት እፈናጠጣለሁ የሚል እንዳለ ያየነው ነው። ዘንድሮ የመሳሪያ ትግሉን እንተወው የሚልን ግለሰብ የሚደረጉት ሁሉ መልካም ናቸው ብሎ እንደተቀበለ መውሰድ ስህተት ይሆናል። ቁም ነገሩ ልዩነታችንን በጠመንጃ መፍታት እናቁምና በውይይት የመፍታት ባህል እናዳብር ለማለት እንደሆነ ይሰመርበት። “የለም መንግሥት የተቃውሞን መግለጫ መንገዶችን ስለዘጋ አማራጩ የትጥቅ ትግል ብቻ መሆን አለበት” ለሚሉት ከዳንኤል አባባል ልዋስና ”በሲኦል በኩል ወደ መንግሥተ ሰማያት የሚወስድ መንገድ የለም“ ልበላቸው።

ለዚህ ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ ባገራችን ስላለው ሁኔታ የሚጻፉትን ጽሑፎች ሳነብ ከሰነበትሁ በኋላ ነው። በሃገራችን የተፈጠረውን እረብሻ አስመልክቶ በአይጋ ፎረም ይጻፉ የነበሩትን አንብቤ በተለይም በአማራው ክልል ባለሥልጣናት ላይና በድርጅቱ በባአዴን ላይ ተሰንዝረው ለነበሩት ጤና አልባ ጽሁፎች በወቅቱ አገርቤት ሆኜ የተሰማኝን የተናገርኩ ስለሆነ መድገም አልፈልግም። የአይጋም አታሚዎች ይቅርታ ባይጠይቁም ትክክል እንዳልነበረ የተቀበሉበትን ለታዳሚዎቻቸው አይለምደንም አይነት በድሕረ ገጻቸው መለጠፋቸውን አስታውሳለሁ። ዛሬ ደግሞ በትግራይ ኦን ላይን እየተለጠፉ ያሉትን ጤና ጎደል ጽሑፎች ሳይ ደነገጥኩ። ለምን ቢሉ ሲኒማ ቤት ተቀምጦ ”እሳት እሳት“ ብሎ መቀለድ አለመቻሉን እንዴት አይገነዘቡም ከሚል በመነሳት ማለቴ ነው ።

ለግንዛቤ እንዲረዳ አንዱን ጽሑፍ ልውሰድ። ጽሑፉ በእንግሊዘኛ ቢሆንም መልሱን አፍ በፈታሁበት ቋንቋ ለመመለስ ወደድኩ። እንደልቤ እራሴን እንድገልጽም ይረዳኛልና። በትርጉም ላይ ያለ መዛነፍን ለማጥፋት ግን ጽሑፉን በእንግሊዘኛ እንዳለ አሰፍረዋለሁ።

ከእርእሱ እንጀምር ሁሉንም ያካትታልና

የ5ኛ አረድፍ የሆኑት አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ተለቀው እየጋለቡ ነው። ይላል

Gedu Andargachew: A fifth column on the loose

http://www.tigraionline.com/articles/gedu-andargachew-5column.html

5ኛ አረድፍ፥ ማለት እንደሚገባኝ ከትልቁ 4 አረድፍ ሰልፈኛ የተገነጠለ በውስጥ ወዳጅ መስሎ የወዳጅን አሰላለፍ የሚያጠቃ ከሰልፉ ያፈነገጠ። በህቡእ የሚንቀሳቀስ፡ ከጠላት በላይ ጠላት የሆነ ማለት ነው። ይህ 5ኛ አረድፍ የሚለው ቃል መጠቀም የተጀመረው በ 1936 የአውሮፓውያን አቆጣጠር የስፓኒሽ የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት እንደነበረ ሲነገር አባባሉን በመግለጫ መልክ የተገለገሉበት ጄነራል ኢሚሊዮ ሞላ GENERAL EMILIO MOLA እንደሆኑ ይነገራል። ጄነራሉ ከጋዜጠኛ ለቀረበላቸው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ የተጠቀሙበት ያገላለጽ ዘይቤ መሆኑ ሲነገር በወቅቱ እሳቸው በአራት አረድፍ የተዋቀረ ጦር ይዘው ወደ ማድሪድ ሲገቡ የከተማው ነዋሪ ሕዝብ ደጋፊ ሆኖ  የተባበረውን 5ኛ አረድፍ ጦር ብለው መናገራቸውን መነሻ ያደረገ መሆኑ ይተረካል። በኋላ ይህ the 5th colum የሚለው አባባል ተቀይሮ ከዋናው ሰልፍ የወጣ ለማለት መጠቀሚያ ሆኗል። ይህንን አባባል ታዲያ ዛሬ አቶ ብርሃን ካሳይ ከላይ በጠቀስነው እርእስ የአማራውን ክልል ባለስልጣናት ለመወንጀል የተጠቀሙበት የክልሉ ባለስልጣናት በሳቸው ትንታኔ ከሰልፉ ወጥተው ከጠላት ጋር አብረዋር ብለው ለማሳመንና ለመወንጀል ከተሳካላቸውም ግለሰቦቹ ላይ እርምጃ ለማስወሰድ የተጠቀሙበት ይመስላል። አቶ ብርሃን እንዲህ ብለው ጽሑፋቸውን ይጀምራሉ።

Gedu Andargachew should have been dismissed from office a long time ago for complicity in the unrest that was ignited in some parts of Amhara region. To expect him to vacate his seat on his own volition as Muktar Kedir and Asther Mamo did in Oromia region, would have been too much to expect from a disreputable human being devoid of basic integrity.

ባጭሩ የሚሉት ክቡር አቶ ገዱ አንዳርጋቸው በአማራው ክልል በተፈጠረው አረብሻ እጃቸው ስላለ ከስልጣናቸው ድሮ መባረር ነበረባቸው። እኚህን ክብር የጎደላቸውን  እምነት የሞራል ብቃት የሌላቸውን ግለሰብ  እንደ ኦሮሞ መሪዎች በፈቃዳቸው ስልጣን ይለቃሉ ብሎ መጠበቅ ስህተት ነው። የሚል ሲሆን ጸሃፊው በመቀጠል .......Tigrians fought and defeated the most powerful army in black Africa and placed Ethiopia among the fastest growing economies in the world. If it was not for the Tigrians, the likes of Gedu and the stout Demeke would not have been where they are today.

ትግሬዎች በጥቁር አፍሪካ ጠንካራ የተባለውን ጦር ተዋግተው በመደምሰስ ኢትዮጵያን በፈጣን ኢኮኖሚ እድገት ካሳዩ የአለም ሀገራት አንዷ እንድትሆን አድርገዋታል። ትግሬዎች ይህንን ባያደርጉ ኖሮ እንደ ገዱና ድብልብል ደመቀ አይነቶች ዛሬ አሉበት ቦታ ላይ አይደርሱም ነበር። ይላሉ።

ይህን ሳነብ ፈራሁ ጽሁፉን መጨረስ ከበደኝ። የአእላፍ የኢትዮጵያ ልጆች በትግል የፈሰሰ ደም ደመ ከልብ ነው ሲባል ስሰማ፡ ትግሬ ነጻ ባያወጣችሁ ኖሮ የሚል ትምክህት ሳነብ ጸሐፊው ሊያበጣብጡ የተነሱ 5ኛ አረድፍ እራሳቸው መሆናቸው ተገለጠልኝ። ማንም ኢትዮጵያዊ የበታች ሆኖ የተወሰኑ የሚኩራሩባት፣ ቀሪዎች የሚሰደቡባት ኢትዮጵያ እንደማትኖር ለወንድሜ  ልነግራቸው ተነሳሁ። በሳቸው ብእር የትግራይን ሕዝብ መገምገም አልፈልግምና፣ የትግራይን ሕዝብ እኔም እንደሳቸው አውቀዋለሁና፣ ለሕዝቡ ያለኝን ፍቅርና  አክብሮት በሳቸው ተራ አመለካከት እንደማላጨልመው በመንገር ጽሑፉ የእሳቸውን የከሰረ የግለሰብ አመለካከት የሚያሳይ ተራና እንጭጭ መሆኑን ሳልነግራቸው ማለፍ ግን አልፈለግሁም። ወንድሜ ትምህርት የቀሰሙ፣ ቋንቋ እንጂ እውቀት የሌላቸው መሆናቸውን ለመገመት ደግሞ ለአንባቢ ግዜ አይፈጅበትም ብዬም አመንኩ። ስለቅማንት ትግል የሚነግሩን ጸሃፊ ስለወልቃይት አያገባችሁም ሲሉም አዳመጥኩ።

- Flouting the constitution by denying the Qemant’s right for self-rule;

- Organising Welkait Committee in Gonder to challenge the regional administration of Tigrai;

በእሳቸው አመለካከት የትግራይ ልጅ በመሆናቸው የኢትዮጵያ ጉዳይ ይመለከታቸዋል። የሁሉንም የክልሎችን መሪዎች ሊመርጡም ይፈልጋሉ። ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን ስለሳቸው ክልል ለመናገር መብት የለውም ይሉናል። ለምን በእሳቸው ጠባብ አመለካከት ኢትዮጵያን ነጻ ያወጣው የትግራይ ሕዝብ ስለሆነ። ወንድሜ ቢገባዎት የቆየ አባባል ልናገር ” ተቅማጥ የያዘው ሰው እንቆቆ አይጠጣም“ ይባል ነበር። ለማለት የፈለኩትን የሚያውቁና የገባዎ ይመስለኛል። ተረዱኝ ? ለግንዛሬ ይረዳዎት ዘንድ የተፈናቀሉት የትግራይ ተወላጆች በትግራይ ምድር የተናገሩትን የምስክርነት ቃል ፈልገው እንዲያዳምጡት ልጠቁምዎ። የአማራው ክልል ሽማግሌዎች ትግራይ ሄደው ያደረጉትን ውይይት ፈልገው ያዳምጡትና ለውይይት የሰሙትን ይንገሩን። እርግጠኛ ነኝ ከዚያ በኋላ በተናገሩት ያፍራሉ ብዬ አስባለሁ።

በተረፈ ክልሎችን ማ እንደሚመራቸው ማ እንደሚያስተዳድራቸው እራሳቸው ይጨነቁ እርስዎ መምረጥም መወሰንም እንደማይችሉ ይቀበሉ። ሰው እንደቤቱ እንጂ እንደ ጎረቤቱ አይኖርም ይባል የለ።

አቶ ብርሃንን የምጠይቃቸው እሳቸው ከሳሽ፣ እሳቸው ተሳዳቢ፣ እሳቸው ፈራጅ፣ እሳቸው ሿሚና ሻሪ፣ ከሆኑ ፍትህ እንዴት ይገኛል ብለው አሰቡ ? ብዬ ነው። ያውም በማያገባቸው ክልል። ድርጅቱ ይወክለኛል ያለውን የአመራር አባላት፣ ሕዝቡ ይመሩኛል ያላቸውን መሪዎች እንዴት ቢንቁ ነው ቃል አቀባይ ወይም ትርጁማን ካልሆነም አቦካቶ ሊሆኑ የተነሱት ? እሳቸው ደጋግመው እንደነገሩን ትግሬ ስለሆኑ ከማንም በላይ ነኝ ብለው አስበው ይሆን ?

አቶ ብርሃን የትግራይ ሕዝብ እንደእርስዎ አይነት አመለካከት የሌለው፣ በኢትዮጵያዊነቱ የሚኮራ፣ በመከባበር የሚያምን፣ ፈሪሃ እግዚአብሐር የተላበሰ እንደሆነ ልነግርዎ እወዳለሁ። ደግ እሩህሩህና አዛኝ ለመሆኑም ቋሚ ምስክር ነኝ። የእርስዎን አባባል ብርጭቆ ውስጥ ባለ ውኃ ላይ እንደተጨመረ አሸዋ ሕዝቡን ደግሞ በዛው ብርጭቆ ውስጥ እተደባለቀ ዘይት አድርጌ ብመስለው ደስ ባለኝ። እንደ እርስዎ አለመዝቀጡን ለማሳየት ማለቴ ነው።

አቶ ብርሃን ለመፈቃቀር መከባበር መኖር እንዳለበት ይቀበሉ። ካልሆነ የባእድ ቋንቋ እየተናገሩ መከረምዎ ነው። ከሁሉም የበለጠ ማለት የምፈልገው ነገር ቢኖር ይህንን መረጃ የጎደለው የስም ማጥፋት ዘመቻ ሲጀመር ተሐሕትም ሆነ የክልሉ ተወላጆች በዝምታ መመልከታቸው ነው። “የግለሰብ አስተያየት ስለሆነ መልስ መስጠት አይኖርብንም ይሉ ይሆናል” ብዬ እገምታለሁ። ይህ እየቀረበ ያለው ክስ ግን አስተያየት ሳይሆን ወንጀል ተፈጽሟል የሚል ስለሆነ መልስ የሚሻ ነው። አቶ ብርሃንም የሰማሁትን ጻፍኩ እንጂ ለውንጀላው መረጃ የለኝም ሊሉ እንደሚችሉም ጠረጠርኩ። ለዚህ ደግሞ የትግራይን የቆየ አባባል ላስታውሳቸው “የሚበቃትን ያክል ፈጭታ ይቅርብኝ ዛሬ ማርያም ነች” አለች የሚለውን። እርስዎ በትግርኛ ይበሉት። በስድብ ማንንም ማስተማርም ሆነ መቀየር አይቻልም። መናናቅና መናናቅ ቢደመር ከመናናቅ ውጭ ምንም መሆን አይችልም። ከመናገራችን በፊት የምንናገረው ምን ያመጣል ብሎ ማሰብ አዋቂነት ነውና አስበን እንናገር ተከባብረንም እንኑር።

ሰናይ እለት

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር ! ! !